

የሮም: ሪፐብሊክ

– ከክርስቶስ፡ ልደት፡ ክ509፡ አ.አ፡ በፊት፣ ሮም፡ ሪፐብሊክ፡ ሆነች። የመጨረሻው፡ ንጉሥ፡ ከወረደ፡ በኃላ፡ በተመረጡ፡ ባለሥልጣናት፡ መመራት፡ ጀመረች። የተመረጡ፡ ባለሥልጣናት፡ ሴናተሮች፡ [Senators]፡ ይባሉ፡ ነበር።

– ለ500፡ ዓመታት፡ ያህል፡ ጥንቷ፡ ሮም፡ በሪፐብሊክ፡ ስርአት፡ ተዳድራ፡ የነበረ፡ ሲሆን፡ ይህ፡ ስረአት፡ ህዝቡ፡ ህጋዊ፡ ባለስልጣናትን፡ እንዲመርጡ፡ አስችሏል። ውስብስብ፡ የሆነው፡ መንግስት፡ ነበር፣ ነገር፡ ገን፣ በህገ–መንግስት፣ ዝርዝር፡ ህጎች፡ እና፡ በህጋዊ፡ መንገድየተመረጡ፡ ሴናተሮች፡ ነበሮት። የተለያዩ፡ ሀሳቦችና፡ የመንግሥት፡ መዋቅሮችም፣ ለዘመናዊ፡ ዴሞክራሲ፡ መሠረትን፡ ጥሎ፡ አልፏል።

የሮም፡ ሪፐብሊክ፡ መሪዎች፡ እነማን፡ ነበሩ?

– በሮም፡ ሪፐብሊክ፡ ውስጥ፡ በርካታ፡ መሪዎች፡ እና፡ ቡድኖች፡ አብረው፡ ያስተዳድራሉ። የተመረጡ፡ መሪዎች፡ እና፡ ባለስልጣናት፡ የተለያዩ፡ የስልጣን፡ ደረጃዎች፡ እና፡ ማእረጎች፡ ነበሩአቸው።

በሮም፡ መንግስት፡ ውስጥ፡ የነበሩ፡ የስልጣና፡ ደረጃዎችና፡ ማእረጎች፡ በጥቂቱ፡ እንመልከት።

➤ ቆንሲልስ፡ [Consuls]፧– በሮም፡ ሪፐብሊክ፡ ውስጥ፡ የበላይ፡ ስልጣን፡ ያላቸው፣ ቆንሲልስ፡ ሲሆኑ፡ ስልጣናቸውን፡ ያለ፡ አግባብ፡ እንዳይጠቀሙ፡ (አምባገነን፡ እንዳይሆኑ)፡ ሁልጊዜ፡ ሁለት፡ ቆንሲልስ፡ ነበር፡ የሚመረጡት። ስልጣን፡ ላይ፡ የሚቆዩትም፡ ለአንድ፡ ዓመት፡ ብቻ፡ ንው፡ ሁለቱ፡ ቆንሲልስ፡ ያልተስማሙበት፡ ነገር፡ ካለ፡ ድምፅን፡ በድምፅ፡ የመሻር፡ [Veto፡ Power]፡ ሙሉ፡ መብት፡ ነበራቸው። በተጨማሪም፡ ከነበሯቸው፡ ስልጣኖች፡ መካከል፣ ጦራንት፡ ማወጅ፣ ምን፡ ያህል፡ ግብር፡ መሰብሰብ፡ እንዳለባቸው፡ እና፡ ህጎች፡ ምን፡ መሆን፡ እንዳለባቸው፡ መወሰን፡ ይችላሉ።

➤ ሴናተርስ፡ [Senators]፧– ሴናተሮች፡ የተከበሩ፡ የመሪዎች፡ ስብስብ፡ (ቡድን)፡ ሲሆኑ፡ በዋናነት፡ ለቆንሲልስ፡ የማማከር፡ ስራ፡ ነበር፡ የሚሰሩት። ቆንሲልሶቹም፡ ከሴናተሮች፡ የሚደርሳቸውን፡ ምክር፡ ነበር፡ የሚፈፅሙት። ሴናተሮች፡ ይህንን፡ የስልጣን፡ ደረጃ፡ እና፡ ማእረግ፡ ይዘው፡ የሚቆዩት፡ እስከሚሞቱ፡ ድረስ፡ ነበር።

➤ የፕሊቤያን፡ ምክር፡ ቤት፡ [Plebeian፡ Council]፦ ይህ፡ ምክር፡ ቤት፡ ሕዝባዊ፡ ጉባኤ፡ በመባል፡ ይጠራ፡ ነበር። በዚህ፡ ምክር፡ ቤት፡ ተራው፡ የሮም፡ ህዝብ፡ (ፕሊቤያን)፡ የራሳቸውን፡ መሪዎች፡ እና፡ ዳኞች፡ የሚመርጡበት፣ ህጎችን፡ የሚያወጡበት፡ እና፡ የፍርድ፡ ቤት፡ ስራ፡ የሚሰሩበት፡ ነበር።

➤ ትሪቡንስ፡ [Tribunes]፦ ትሪቡንስ፡ የፕሊቤያን፡ ምክር፡ ቤት፡ ተወካዮች፡ ነበሩ። በተጨማሪም፡ በሴኔት፡ የተደነገጉ፡ ህጎችን፡ የመመለስ፡ ስልጣን፡ ነበራቸው።

➤ ገዢ፡ [Governors]፦ የሮም፡ መንግስት፡ አዳዲስ፡ መሬቶችን፡ ድል፡ አድርጎ፡ ሲቆጣጠር፡ ለአዲሱ፡ ግዛት፡ ወይም፡ መሬት፡ ገዢ፡ በሴኔቱ፡ አማካኝነት፡ ይሾማል። ይህ፡ የተሾመው፡ ገዢ፡ በአካባቢው፡ ላለ፡ ጦር፡ አዛዥ፡ እና፡ ግብር፡ መሰብሰብ፡ ሀላፊነት፡ ነበረው።

➤ አድል፡ [Aedile]፦ እነዚህ፡ የከተማ፡ ባለስልጣናት፡ ሲሆኑ፡ ሀላፊነታቸውም፡ የህዝብ፡ ሕንጻዎችን፡ መጠገን፣ ህዝባዊ፡ በዓላትን፡ ማካሄድ፣ ገቢያዎችን፡ መሰብሰብ፣ የእህልና፡ የውሃ፡ አቅርቦትን፡ መቆጣጠር፡ ነበር። ብዙ፡ ፖለቲከኞች፡ ለከፍተኛ፡ ስልጣን፡ (ቆንስል)፡ እንዲመረጡ፡ ከፈለጉ፡ በመጀመርያ፡ አድል፡ [Aedile]፡ በመሆን፡

ሕዝባዊ፡ በአላትን፡ ለህዝቡ፡ በማዘጀት፡ በሕዝቡ፡ ዘንድ፡ ተወዳጅነት፡ ለማትረፍ፡ ይጥሩ፡ ነበር።

➤ ሴንሰር፡ [Censor]፡– ዜጎችን፡ የመቁጠር፡ ሀላፊነት፡ የተጣለባቸው፡ ባለስልጣናት፡ ነበሩ።

የሮም፡ ህገ–መንግስት

– የሮም፡ ሪፐብሊክ፡ ምንም፡ እንኳን፡ የተፃፈ፡ ህገ–መንግሥት፡ ባይኖራትም፡ ከትውልድ፡ ወደ፡ ትውልድ፡ የሚተላለፉ፡ መመሪያዎችን፡ ነበር፡ ተግባራዊ፡ የሚያደርጉት።

ሁሉም፡ ሰዎች፡ በእኩል፡ ተስተናግደው፡ ነበር?

– በፍፁም፣፡ በሰዎች፡ ላይ፡ በሀብት፣ በጾታ፡ እና፡ በዜግነት፡ ደረጃ፡ ላይ፡ የተመሰረተ፡ አድሎ፡ ሲፈፀም፡ ነበር።። ሴቶች፡ የመምረጥ፡ መብት፡ አልነበራቸውም።። እንዲሁም፡ ገንዘብ፡ ያለቸው፡ ሰወች፡ ብዙ፣ ድምፅ፡ የመስጠት፡ እድሉ፡ ነበራቸው።። በሮም፡ ውስጥ፡ መደበኛው፡ ህዝብ፡ አንድ፡ ላይ፡ በመሰብሰብ፡ ምክር፡ ባቱ፡ ላይ፡ ከፍተኛ፡ ኃይል፡ የኖራቸው፡ ነበር።

@nebeb_ethiopia, ንበብ፡ ኢትዮጵያ